**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (የካቲት 9፣ 2000 ዓ. ም.)**

**ወያኔና ሻዕቢያ ጦርነት መጀመራቸው አይቀሬ ይመስላል፣ ወያኔ በቆሰቆሰው የእርስ በርስ ግጭት ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ 52 ሰዎች ተገደሉ፣ ተማሪዎች ተቃውሞ ያነሳሉ በሚል ፍራቻ አገዛዙ አዲስ ሰልት ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው፣ ጣና ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮችን ለማፈናቀል እነአዲሱ ለገሰ የወጡት እቅድ በህዝቡ ቆራጥነት ከሸፈ፣ ከመለሰ በተሰጠው ትዕዛዝ አዲሱ ለገሰ ስለ ሕወሓት አመሰራረት በትግርኛ መግለጫ ሰጠ፣ አሜሪካዊው ባለወረት ከ3 ሚሊዮን ብር በላይ ከሰሩ፣ የፖስታ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ከስራቸው ተባረሩ፣ የሕወሓቱም ካድሬ ተኳቸው፣ ጁነዲ ሳዶ ስብሰባ ረግጠው ፈረጠጡ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ**.................................

የወያኔና የሻዕቢያ ቡድን ወደ ጦርነት መግባታቸው አይቀሬ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች እየታዩ መሆኑን አለም አቀፍ ሚዲያዎች እየገለፁ ናቸው::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ የሠላም አስከባሪው ኃይል ከሰፈረበት ድንበር ላይ ነቅሎ ጦሩን ያስወጣ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ ሻዕቢያ ጦሩን ወደ ኢትዮጵያ ድንበር እያስጠጋ ዋና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች የተባሉትን ኮረብታዎች መቆጣጠሩም ተዘግቧል::

የወያኔ ቡድንም በበኩሉ በተለያዩ ቦታዎች አስፍሯቸው የነበሩትን የጦር ክፍሎች እየቃረመ ወደ ድንበሩ የወሰደ በመሆኑ ሁለቱ ቡድኖች ጦርነቱን በቅርቡ ሊጀምሩ እንደሚችልም ይጠበቃል::

እንዲህ ከሻዕቢያ ጋር ተፋጥጦ ውጊያ ለመጀመር በተዘጋጀበት በዚህ ወቅት የወያኔው ቡድን በደቡብ ክልል ሕዝቡን በተሳሳተ መንገድ እየቀሰቀሰ እርስ በእርስ እንዲገዳደል እያደረገ መሆኑ ታውቋል::

በዚህም መሠረት የወያኔ መሰሪ ቡድን በሚዘረጋው ከፋፍለህ ግዛ የተነሳ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በደቡብ ክልል ውስጥ በሚከሰተው የእርስ በእርስ ግጭት በርካታ ሰዎች እየሞቱ ቤት ንብረታቸው እየወደመ ለስደትም እየተዳረጉ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ባለፈው ሳምንት ከጥር 25 ቀን እስከ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በደራሼ ልዩ ወረዳ ውስጥ በተከሰተ የእርስ በእርስ ግጭት ከ52 ሰዎች በላይ ለሞት የተዳረጉ ሲሆን በርካታ ቤቶችም እንደወደሙ የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

በደራሼ ልዩ ወረዳ ውስጥ በኮንሶ አዋሳኝ 5 ቀበሌዎችና አዲስ ኦፕቴም የሚባል ቀበሌ ነዋሪዎች በአንድነት ሆነው ከደራሼ ብሔር ተወላጆች ጋር በፈጠሩት ፀብ 34 ሰዎች ከሁለቱም ወገን የሞቱ ሲሆን፣ 18 የፌዴራልና የወረዳው ፖሊሶችም እንደተገደሉ የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

ወያኔ ሕዝቡን እርስ በእርስ እያጋጨ በሕዝብ እልቂት የሚደሰት አይን የሌለው እውር፣ እጅ የሌለው ጉምድ፣ እግር የሌለው ቆራጣ የሆነ ቡድን መሆኑን የተመሰከረለት በተንኮል የተካነ መሰሪ ቡድን ነው ያሉት የአካባቢው ተወላጅ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር ለዘመናት ተከባብሮና ተዋልዶ የኖረውን ሕዝብ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲል ብቻ ወያኔ ከ52 ሰዎች በላይ ሕይወታቸው እንዲያልፍ ማድረጉ በጣም የሚያሳዝንና የሚያንገበግብ ነው ሲሉ በንዴት ገልፀዋል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በተደጋጋሚ ጊዜ ወደ ደቡብ የተለያዩ ዞኖች እየተዘዋወረ ጉብኝት እያደረ ከመሆኑም ባሻገር ብጣሽ ጨርቅ እየሰጣቸው ለማታለል ሙከራ እያደረገ መሆኑን የገለፁት እኚሁ መምህር «የአክሱም ሐውልት ለደቡቡ ምኑ ነው?» ብሎ እንዳልነበር መለስ ለኛ ምናችን ስለሆነ ነው በየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ እንደተራ የወረዳ ካድሬ በየመንደሩ የሚዞረው? ብለን አጥብቀን ልንጠይቀው ይገባል ብለዋል፡፡

አክለውም በደቡብ በሁሉም ወረዳዎች ማለት ይቻላል ግጭቶችና የእርስ በእርስ እልቂቶች በካድሬዎች መሰሪ ተግባር የተነሳ እየተካሄደ መሆኑን እያወቀ የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ስለ ጉዳዩ አንዲትም ነገር ትንፍሽ ሳይል የሐሰት የልማት ፕሮፓጋንዳውን እያናፈሰ መሆኑን እኚሁ መምህር በንዴትና በቁጭት ገልፀዋል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ ጊዜ ወደ ደቡብ ክልል በመንዝ እስከ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ድረስ የአርሶ አደሩን ኑሮ ሊመለከት የገባ በማስመሰል የሐሰት ድራማ ያካሂድ እንጂ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሣራ የደቡብ ክልል



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሕዝቦች ድጋፍ አግኝቶ እጠገናለሁ በሚል እሳቤ እየዞረ መሆኑንም አንዳንድ የፖለቲካ ምሁራኖች ይገልፃሉ፡፡

ለስሙ ከአርሶ አደሩ ተመርጠው የመጡ ናቸው የተባሉ አንዳችም ሐሳብ የማያቀርቡና ወንበር አሙቀው የሚውሉት የወያኔ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ስለጉዳዩ አንስተው አንዳችም ትንፍሽ ያላሉ ከመሆኑም በላይ ስለሞቱትና ቤት ንብረታቸው ወድሞባቸው ያለመጠለያ ስለተበተኑት ሕዝቦች ምንም የማይሰማቸው ልበ ድንጋይ መሆናቸውን ያሳያል ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ በሌሎች የደቡብ ወረዳዎች ውስጥ በርካታ ግጭቶች ተነስተው የነበረ ቢሆንም በደራሼና በኮንሶ መካከል ከጥር 25 ቀን እስከ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም ለተከታታይ 3 ቀናት የተካሄደው ይኸው ግጭት በጣም ከባድና ሰቅጣጭ መሆኑንም ስንሰማ በጣም አሳዛኝና የወያኔ ርካሽ ተግባር መሆኑን ስንረዳ ልባችን በሀዘን ተነክቷል በማለት ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ቡድን በደቡብ ክልል ይህንን የመሰለ አይን ያወጣ በደልና ግፍ በሕዝቡ ላይ እየፈፀመና ሕዝቡ እርስ በእርስ ተደጋግፎና ተሳስቦ እንዳይኖር ምክንያት እየፈጠረ እያጋጨና ሕዝቡ እያለቀ ባለበት በዚህ ወቅት በትግራይ ክልል ግን የሕወሓትን 33ኛ ዓመት ምስረታ በዓልን አስመልክቶ የተጣሉ ሁሉ እንዲታረቁ የሚያስገድድ ትዕዛዝ ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ከወያኔው ካድሬ ፀጋዬ በርሄ መውጣቱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

በትግራይ ክልል ውስጥ በትንሽም ሆነ በትልቅ ጉዳይ የተጣሉ የትግራይ ተወላጆች በመሀላቸው የያዙትን ፀብ አቁመው እርቅ እንዲያወርዱ የሚያስገድደው ይኸው ትዕዛዝ ጉዳያቸው በፍ/ቤት የተያዘ በመሉ ፋይላቸው ተዘግቶ በሠላማዊ መንገድ እንዲያልቅና ሕዝቡ እርስ በእርሱ እንዲተባበርና እንዲፋቀር ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

በዚህም መሠረት በትግራይ ክልል በአክሱም ዞን በላዕላይ ማይጨው ወረዳ ውስጥ እርስ በእርስ ተጣልተው ጉዳያቸው በፍ/ቤት ተይዞ የነበሩትን ከ600 በላይ ሰዎች በሐገር ባህል ወግ እንዲታረቁ ያደረገ መሆኑን ይኸው ዘገባ ጠቁሞ በትግራይ ይህን የመሰለ ጉዳይ ሲፈፅም በሌላው አካባቢ ደግሞ እርስ በእርስ እንዲተላለቁ ማድረጉ በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳፍር መሆኑን ዘገባው አስረድቷል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በሌላው ክልል እጅግ በጣም የሚያሳዝን ታሪክ እየፈፀመ ያለው ወያኔ በደቡብ ውስጥ ሕዝቦች በቀየኑ እንደቅጠል ሲረግፉ አንዲትም ነገር ትንፍሽ ያላለ ሲሆን በአንፃሩ በትግራይ ውስጥ በረባውም ሆነ ባልረባው በግለሰቦች መካከል የተነሳን ግጭት እንዲወገድና እንዲታረቁ አድርጐ ሕግ የያዘውን ፋይል እየዘጋ መሆኑን የገለፀው ዘገባው በአንድ ሐገር የተለያየ ሕግ መኖሩን የሚያሳይ ነው ሲልም አብራርቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጉራጌ፣አማራ፣ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ቤንሻንጉል፣ ወላይታ . . . ሳይል እርስ በእርስ ተፋቅሮ እና ተዋድዶ የኖረውን ሕዝብ ወያኔ የትግራይን አክሱም ለወላይታምኑ ነው? እያለ እርስ በእርስ እንዲቃቃርና በአይነ ቁራኛ እንዲጠባበቅ ከማድረጉም ባሻገር ንፁሃን የትግራይ ልጆች በሌሎቹ ብሔሮች እንዲጠሉ ሆን ብሎ እየሰራ መሆኑን ተረድተናል ሲሉ አንድ የትግራይ ብሔር ተወላጅ የሁለተኛ ደረጃ መምህር ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ዛሬ ወያኔ ከሕዝብ የተተፋ መሆኑን ያወቀ በመሆኑ በአንዳንድ ሆድ አደር የትግራይ ልጆች ጀርባ ታክኮ የራሱን ሕልውና ለማስጠበቅ ከላይ ታች እየተራወጠ እና ለዘመናት ተቃቅፈን የኖርነውን የሐገሪቷን ዜጐች ተቧድነን እንድንጋጭ ለማድረግ እየሮጠ ስለሆነ ይህንን ተልካሻና የማይረባ ሥራ ተግባራዊ ከማድረጉ አስቀድሞ መላው የሐገሪቷ ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘን ልናከሽፈው ይገባናል ሲሉም እኚሁ መምህር መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በሁሉም መስክ የፖለቲካ ትርፍ ያስገኙልኛል የሚላቸውን ተግባሮች ከመፈፀምና ከመኮነን ወደ ኋላ የማይለው ወያኔ በደቡብ ውስጥ እራሱ ቀስቅሶ ለተከሰተው እልቂት መፍትሄ ሳይሰጥ እንደገና በየትምህርት ቤቱ ተማሪው እምነቱን ጠብቆ እንዳይታነፅ ለማድረግ ትልቅ ደንቃራ ፈጥሮ የነበረ ቢሆንም በተማሪዎቹና በወላጆቻቸው ብርቱ ድጋፍ ችግሩ ሊቃለል የቻለ ቢሆንም አሁንም ደግሞ ሰሞኑን በየትምህርት ቤቱ የተማሪዎች መማክርት እንዲቋቋም በማለት መመሪያ ማስተላለፉ ከየትምህርት ቤቱ የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

እንደደረሰን ዘገባ ከሆነ ወያኔ የስልጣን እድሜውን ለማራዘሚያ ብሎ የነደፋቸው ስልቶች ሁሉ እየተነቁበት ፉርሽ ቢሆኑበትም ሰሞኑን በተማሪዎች መካከል ሰላይ ለማሰማራት እቅድ ስላለው የተማሪዎች መማክርት ምክር ቤት መቋቋም አለበት በማለት መመሪያ ማስተላለፉ ታውቋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በዚሁ ወያኔ በነደፈዉ ስልት በየትምህርት ቤቱ ለስለላ ተግባር የተመለመሉ ተማሪዎችን የመማክርት ኮሜቴ አባላት በማድረግ በመማክርት ምክር ቤት ስም መምህራኑን ጨምሮ ተማሪዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በስለላ መልክ ለሚመደቡበት ዞን የደህንነት ቢሮ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ለማድረግ ታቅዶ የተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተለይም በአሁን ሰዓት በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት አሻቅቦ ሕዝቡ የእለት ጉርስ መቅመስ አቅቶት በተቸገረበት ጊዜ ተማሪዎች ይህንኑ ጉዳይ አንስተው ተቃውሞ ሰልፍ ያካሂዳሉ በሚል ስጋት አዲስ ስልት ነድፎ ተማሪዎችን ለማቆጣጠር ያቀደው መሆኑን አንዳንድ ወገኖች እየገለፁ ናቸው፡፡

ወያኔ ምንም እንኩዋን አዲስ ስልት በነደፈው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ ለየትምህርት ቤቶቹ ትዕዛዝ ቢሰጥም የአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን «እኛ አስቀድመን ተማሪዎች እና መምህራን ያሉበት ኮሚቴ አዋቅረን እየሰራን ስለሆነ ይህ የተማሪዎች መማክርት ኮሚቴ ይቋቋም የሚለውን አንቀበለውም» በማለት ከፍተኛ ተቃወሞ እያሰሙ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቷል፡፡

ወያኔ እንደ ጋሪ ፈረስ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ተመልክቶና እኔው ልንዳችሁ በማለት የያዘውን ግትር አቋም በአንዳንድ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና መምህራኖች እምቢ ባይነት የመማክርት ምክር ቤት ለማቋቋም እንዳልተቻለ የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነፃ የሆኑ ርዕሰ መምህራኖች ይህንን አቋም ደግፈው በፅኑ እየተቃወሙት መሆኑንም አብራርቷል፡፡

በሌላ በኩል ለዘመናት ከአያት ቅደመ አያቶቻቸው ጀምሮ ሲወርድ እና ሲዋረድ የመጣውን የመሬት ይዞታ የወያኔ ካድሬዎች እንዲለቁ ትዕዛዝ የሰጡ ቢሆንም አርሶ አደሮቹ አሻፈረኝ በማለታቸው የካድሬዎቹ ሙከራ ሊከሽፍ እንደቻለ ከባህርዳር የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ባለፈው ወር ውስጥ በባህርዳር ጣና ዙሪያ ሰፍረው ያሉትን ገበሬዎች በትንሽ ገንዘብ ከቦታቸው ለማፈናቀል የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ነው የተባለው ቀንደኛው የወያኔ አሸርጋጅ ዮሴፍ ረታ እና የብአዴን ሊቀመንበርና የሕወሓት ተላላኪው አዲሱ ለገሰ ከነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር አርሶ አደሮቹን ከአካባቢው ለማፈናቀል ከፍተኛ ድካም የደከመ ቢሆንም የአካባቢው አርሶ አደሮች



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

«ከእኛ ቀድሞ አስክሬናችን ካልወጣ በስተቀር ከቀዬአችን ፈፅሞ አንለቅም» በማለት በመዛ ቸው የተነሳ የታቀደው ሁሉ እንደከሸፈባቸው ይኸው ከባህርዳር የደረሰን ዘገባ አስታውቋል::

ለአንድ ሱዳናዊ ባለሀብትና ለአንድ ቱርካዊ ባለሀብት ሁለቱ በጋራ እና በጥምረት በጣና ዙሪያ የሸንኮራ ተክል ለማልማትና የስኩዋር ፋብሪካ ለመትከል ዕቅድ ነድፈው በአየር ላይ ከአማራ ክልል ፕሬዝዳንት ዮሴፍ ረታ እና ከብአዴን አዲሱ ለገሰ ጋር ስምምነት የደረሱ ቢሆንም የአካባቢው ሕዝብ ሴት፣ ወንድ፣ ሕፃን፣ አዋቂ ሳይል መሣሪያ ያለው በመሣሪያ ቆንጨራ ያለው በቆንጨራ ለመፋለም መዘጋጀታቸውን በማወቃቸው ችግርም ከተነሳ መብረጃ እንደሌለው በመረዳታቸው ስምምነታቸው ፈርሶ እንደገና ሌላ አዲስ ስምምነት ለመፈራረም እንደተገደዱና ከጣና ኃይቅ 5 ኪሎ ሜትር ድረስ በቱቦ ለመሳብ እንደተገደዱም ዘገባው አብራርቶ ሕዝቡ በወሰደው ቆራጥ አቋም የወያኔ ተላላኪዎች እቅድ ሊከሽፍ እንደቻለም አብራርቷል::

የወያኔዎቹ ተላላኪዎች ኃይል ለመጠቀም አስበው የነበረ መሆኑን የባህርዳር ምንጮች ገልፀው የሱዳናዊው ባለሀብትና ቱርካዊው ባለሀብት «ዛሬ የዚህን አካባቢ ሕዝብ በጉልበትና በኃይል አነሳስተን ሥራውን ብንጀምርም ነገ በድርጅቶቻችን ላይ አደጋ ሊከሰትና ልናተርፍ መጥተን ከስረን ልንመለስ ስለምንችል ሕዝቡን በፍቅር መያዝ እንጂ በኃይል ተገቢ አይደለም» በማለት ነገሩን በሠላም የጨረሱ ሲሆን ተላላኪዎቹ ግን ድሮም መሣሪያ እያመለኩ አሁንም በዚያው መንገድ ሲጓዙ ማሰባቸው የእውቀት ድውዮች መሆናቸውን ያሳያል ሲሉ እነዚሁ የባህርዳር ምንጮች ገልፀዋል::

ካለፈው ወር ጀምሮ በጥቂት የብአዴን ባለሥልጣናት ላይ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እቀባ ጥሎባቸው የነበረ መሆኑን የቤተ መንግስት ምንጮቻችን ገልፀው ከእነዚህ መካከል አዲሱ ለገሰ፣ በረከት ስምኦን፣ ዶክተር ስንታየሁ የተባለው የትምህርት ሚኒስትሩ የሚገኙበት ሲሆን ከ15 ቀን በኃላ ከማይነፍሱት ጋር የማይነፍስ ብሎ በሕወሓት ክፍፍል ወቅት መለስን ከወድቀት ያዳነው አዲሱ ለገሰ እቀባው የተነሳለት ሲሆን፣ ሰሞኑን ከ1 ወር በኋላ ደግሞ የትምህርት ሚኒስትሩ ዶክተር ስንታየሁ የተባለውም እቀባው እንደተነሳለት የቤተ መንግስት ምንጮች ገልፀው እስከአሁን ከ1 ወር በላይ የሆነው በረከት ስምኦን ግን እንዳልተነሳለት አብራርተዋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የአማራን ሕዝብ እንወክላለን እያሉ በአማራው ሕዝብ ስም እየማሉ እየተገዘቱ ለሕወሓት ቅኝ አገዛዝ የዳረጉት እነዚሁ ተላላኪዎቹ እነ አዲሱ ለገሰ ሕዝቡን እንዲፈናቀል እያደረጉ መልሰው እያፈሱ የጦር ካምፕ ውስጥ እያጐሩ መለመኛ እያደረጉት መሆኑንም ከዚህ ቀደም የዘገብን መሆኑ ይታወሳል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ ይኸው ቀንደኛ የወያኔ ተላላኪ የሆነው አዲሱ ለገሰ ከመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሕወሓት 33ኛ ዓመት በዓልን በማስመልከት በትግርኛ መግለጫ የሰጠ መሆኑ የመወያያ ርዕስ ሆኖ ሰንብቷል፡፡

«በረሀ ቀርፀን ያመጣናቸው ታጋዮች አሉን» ብሎ መለስ ዜናዊ ሲያሞካሻቸው ከነበሩት መካከል አዲሱ ለገሰ አንዱ መሆኑን ያስረዳው ዘገባው በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከእነ መለስ በላይ ስለሕወሓት አመሰራረት በትግርኛ ሲያብራራ መደመጡን ተከትሎ ሕዝቡ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? በማለት አጥብቆ እየጠየቀ መሆኑም ተደምጧል፡፡

የወያኔ የማስመሰያ ፕሮፓጋንዳ እውነት መስሏቸው ውጭ ሀገር ብዙ ዓመታት ቆይተው ለስራ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡት ኢንቨስተሮች መካከል በርካቶች በተለያየ ወያኔያዊ ሰራሽ ችግሮች ምክንያት እየለቀቁ ወደ መጡበት እየተመለሱ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገልፀዋል፡፡

በተለይም የወያኔን ፖለቲካ ደግፈው ከስር ከስር አብረው ካልተከተሉ በስተቀር የመጡበትን የኢንቨስተርነት ተግባር ማከናወን እንደማይችሉ በተለያዩ ቦታዎች በሚፈፀምባቸው ተግባር ያረጋገጡ በርካታ ኢንቨስተሮች በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘባቸውን ሜዳ ላይ በትነው ወደየመጡበት የተመለሱ ሲሆን፣ ሰሞኑን ደግሞ በደቡብ ክልል በእርሻ ልማት ላይ ተሰማርተው የነበሩ አቶ ታሪኩ ካሣ የተባሉ አሜሪካዊ ከ3 ሚሊዮን ብር በላይ በፈጀ ገንዘብ ያቋቋሙት የእርሻ ልማት በአካባቢው በተከሰተው ችግር ምክንያት መሉ በመሉ ልማቱ ሊበላሽ እንደቻለ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በደቡብ ክልል አማሮ ልዩ ወረዳ ውስጥ በጉጂ ኦሮሞ ብሔርና ኮሬ ብሔር መካከል በተከሰተ ግጭት የእርሻ ልማቱ ሙሉ በመሉ የወደመ ከመሆኑም በላይ ለእነ መለስ ኢንቬስተሩ እልባት እንዲሰጣቸው ቢወተውቱም አንዲትም ምላሽ ሳይሰጣቸው እራሳቸውም አካባቢውን ለቀው ወደ አዲስ አበባ መግባታቸውን ታውቋል፡፡ እነ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መለስ ዲያስፖራውን ለማታለል ሲሉ ብቻ በሀገሪቷ ውስጥ ሠላም የሰፈነ በማስመሰል ባዶ ፕሮፓጋንዳቸውን ቢነዙም ይህ ችግር ተከስቶ መፍትሄ መስጠት ተስኗቸው ለብዙ ዓመታት ውጪ ሐገር ለፍተው ያገኙት ገንዘብ በወያኔ መሰሪ ተግባር ባክኖ እንደቀረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የወያኔው ቡድን የአካባቢና የማሟያ ምርጫን ተከትሎ በሕዝቦች ላይ ከፍተኛ በደል እየፈፀመ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

በሐረር፣ በወለጋ፣ በወሎና በሌሎችም አካባቢዎች የወያኔ የወረዳና የዞን ካድሬዎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የሆኑትን ያለምንም ጥፋት እየደበደቡ ለእስር የሚዳርጓቸው ሲሆን፣ ለምርጫ እጩ ሆነው የተመዘገቡት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ደግሞ «ሕገ መንግስቱን በአመፅ ለመናድ ነው» በማለት እያስፈራሩና እያዋከቡ ከውድድሩ እራሴን አግልያለሁ በል እየተባሉ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

በተለይም በወለጋ ውስጥ ተላላኪዎቹ ኦህዴዶች ማንኛውም የከተማ ነዋሪ ለተቃዋሚ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚሆን ቤት ማከራየት የለበትም፡፡ ለመኖሪያነት እንኩዋን ቢፈልጉ ቀበሌ ድረስ ሄደው ካላስፈቀዱ እንዳያከራዩ የተከለከሉ ከመሆኑም በላይ ከተቃዋሚ ፓርቲ አባል ጋር ቆሞ ያወራ ሰው በእስር እንደሚቀጣም ዘገባው አብራርቷል፡፡

ለይስሙላ ምርጫ ይደረጋል ተብሎ አንድም የረባ ተቃዋሚ ፓርቲ በሌለበት በዚህ ወቅት እንኩዋን የወያኔው አረመኔያዊ ቡድን በመፍራት በሕዝቦች ላይ ወከባና እንግልት መፍጠሩ ፓርቲው የብልሹ ግለሰቦች መሰባሰቢያ በመሆኑ በራሳቸው ስለማይተማመኑ አሁንም በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ ሲል ይኸው ዘገባ ገልጿል፡፡

ሕዝቡ በ1997 ዓ.ም ግንቦት 7 ቀን ይሆነኛል ብሎ የመረጠ ቢሆንም የወያኔው ቡድን ሥልጣን በጠመንጃ እንጂ በምርጫ አይሆንም በማለት በፈጠረው አምባገሮ ከ200 በላይ ንፁኃን ዜጐችን በየአደባባዩ በአልሞ ተኩዋሽ ነፍሰ ገዳይ አግአዚ ጦር የገደላቸው ሲሆን፣ ይህንን ጊዜ በማስታወስ ሕዝቡ አልመርጥም ካርድ አላወጣም ቢልም የወያኔ ካድሬዎች ለፕሮፓጋንዳ እንዲሆናቸው በማሰብ እንደቀበሌ ፋሽን በግዳጅ በየቤቱ እየዞሩ የምርጫ ካርድ የሰጡ መሆኑን ያስታወሰው ዘገባው ወያኔ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከአራት ሚሊዮን በላይ እጩዎችን አቅርቢያለሁ እያለ መልሶ በድንጋጤ ሕዝቡን ለከፋ ስቃይ መዳረጉ በጣም አሳዛኝና አስደንጋጭ ነው ሲሉም ሁኔታውን የሚከታተሉ አንዳንድ ምሁራን ይገልፃሉ።

ወያኔ በራሱ ጊዜ የሚፈልጋቸውና በአምሳሉ የቀረፃቸው ከ20 በላይ ተቃዋሚ ፓርቲ ተብዬዎች በአሁን ሰዓት ለምርጫ ውድድር እየተሯሯጡ ያሉት ለእያንዳንዱ ፓርቲ የሚሰጥ ገንዘብ በመኖሩ እሱን ለመውሰድ መሆኑን የምርጫ ቦርድ ምንጮች ገልፀው አንዳንዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሊቀመንበሩና ቤተሰቦቹ ብቻ ያሉበት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል።

እንዲሁም ወያኔ በራሱ አምሳል የቀረፃቸው የተቃዋሚ ፓርቲ ተብዬ ስብስብ መሆናቸውን እያወቀ እንኩዋን በመፍራት ሕዝቡ ላይ እየፈፀመ ያለው ሕገ ወጥ ድርጊት አሳዛኝና አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ቡድኑ ደካማ መሆኑን ቁልጭ አድርጐ ያሳያል በማለት የነቀምት ከተማ ነዋሪዎች በምሬት ይገልፃሉ ።

በመጨረሻም በመንገድ ትራንስፖርት ስር የሚተዳደረው የፖስታ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ከስልጣናቸው መባረራቸውንና በምትካቸው የሕወሓት አባል የሆነው ግለሰብ በቦታው መተካቱን የፖስታ ድርጅት ምንጮች አጋለጡ።

ከየካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ አቶ ተኮላ ሽመልስ የተባሉት የፖስታ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ተባርሮ ከአቅም ግንባታ ቢሮ አቶ ግደይ ገብረዮሐንስ የተባለ የሕወሓት አባል ቦታውን እንዲረከብ የተደረገ ሲሆን አቶ ተኮላ የተባረረው በድርጅቱ ሠራተኞች ላይ የሚያደርሰውን በደል ፊት ለፊት እየተሟገተ ስላስቸገረ መሆኑንም የምንጮቹ ጥቆማ ያስረዳል።

ከ550 በላይ የፖስታ ድርጅት ሠራተኞች በመዋቅር ሰበብ በቅርቡ የተባረሩ ሲሆን፣ ይህንኑ ተከትሎ ዋና ስራ አስኪያጁ ከመንገድ ትራንስፖርት ሚኒስትር አቶ ጁነዲ ሳዶ ጋር በቃላት እየተፋለመ ከፍተኛ ሙግት ያደረገ መሆኑን ምንጮቹ ጠቁመው በኋላም የመደብ ጀርባው ይጠና ተብሎ የአማራ ተወላጅ ሆኖ በመገኘቱ ከስራው ሊባረር እንደቻለና የሕወሓቱ ካድሬ በቦታው እንዲመደብ መደረጉን ይኸው የምንጮቹ ጥቆማ ያስረዳል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በቅርቡ የተባረሩ ከ550 በላይ ሠራተኞች አቶ ጁነዲ ሳዶን እንዲያናግራቸውና ፕሮግራም እንዲይዝላቸው በተደጋጋሚ ግዜ ጥያቄ ቢያቀርቡም እስከአሁን ድረስ ያልተሳካላቸው ሲሆን ሰሞኑን ግን በአስቸኩዋይ ሰብስቦ እንዲያናግራቸው ከረርና መረር ያለ ደብዳቤ ፅፈው የካቲት 5 ቀን 2000 ዓ.ም ሰብስቧቸው እንደነበር ታውቋል፡፡

እነዚህ ከስራ ገበታቸው ላይ በመዋቅር ሰበብ የተሰናበቱ ከ550 በላይ ሠራተኞች አቶ ጁነዲ እንዲያነጋግራቸው ባደረጉት መሠረት ረቡዕ የካቲት 5 ቀን 2000 ዓ.ም ስብሰባውን ረግጦ እንደወጣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የወያኔው ቀንደኛ ተላላኪ ጁነዲ ሳዶ ስብሰባውን መምራት ተስኖት የወጣው ሠራተኞቹ ባለን እውቀትና ሙያ የስራ መደብ ተሰጥቶን መስራት ነው የምንፈልገው በማለት ከረር ያለ ጥያቄ ሲያቀርቡ በመደናገጥ ስብሰባውን ይመራ ከነበረበት አዳራሽ እየሮጠ ጥሎ መውጣቱም ተረጋግጧል፡፡

በተለይ እነዚህ የችግሩ ሠለባ የሆኑት ዜጐች ሲገልፁ አቶ ጁነዲ የራሱን የተደላደለ ሕይወት እየኖረ በእኛ በጭቁኖቹ ላይ ሞት እየፈረደብን ይገኛል፡፡ ፓርኪንግና እና የክበብ ስራ ሰርታችሁ ኑሩ ብሎ መፍረዱ በጣም የሚገርምና የሚያሳዝን ነው ካሉ በኋላ በአሁን ሰዓት የኑሮ ውድነት በሀገራችን ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እየታወቀ በፓርኪንግና በክበብ ስራ ቤተሰቦቻችሁን አስተዳድሩ ብሎ ማለቱ ህሊና የሌለው የጋሪ ፈረስ መሆኑን ተገንዝበናል ሲሉ በእልህና በንዴት ሲገልፁ ተደምጠል፡፡

ከ20 ዓመትና ከዚያም በላይ በዚሁ በፖስታ አገልግሎት ድርጅት ውስጥ ሲሰሩ የቆዩት እነዚሁ ሰራተኞች በቅርቡ ተጠና በተባለው መዋቅር ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተው እያንከራተቷቸው ሲሆን ጁነዲ ሳዶም በያዘው ወልጋዳ አቋም የተነሳ ተፈናቃዮች ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው እንደሚገኙም ታውቋል፡፡ ጁነዲ ሳዶ ማለት የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረና አሁን ትራንስፓርትና መገናኛ ሚኒስትር ሆኖ እያገለገለ ያለ የወያኔ ቱባ ሹማምንት ነው፡፡

የወያኔ ተላላኪና ጉዳይ አስፈፃሚ ነው የተባለው የሱማልያው ፕሬዝዳንት አብድላሂ የሱፍ፣ ማክሰኞ የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብቶ የካቲት 5 ቀን 2000 ዓ.ም መመለሱ ታውቋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በሌላ ዜና የሱማልያው ፕሬዝዳንት አብዳላሂ ዩሱፍ በመለስ ጥሪ እንደመጣና አስፈላጊው ሁሉ እገዛ ተደርጐለት እንደተመለሰ የቤተ መንግስት ምንጮች ገልፀው በወቅቱ ጤንነት ያልተሰማቸው በመሆኑ የወያኔው መሪ መለስ የግል ሐኪም እንዲመለከታቸው መደረጉንም ምንጮች ገልፀዋል፡፡

የሱማልያው ፕሬዝዳንት በከፍተኛ ሁኔታ ሰውነቱ የቀነሰ ከመሆኑም በላይ ለረጅም ሰዓት መቆም እየተቸገረ እንደ ፕሬዝዳንት ግርማ አሁንም አሁንም ቁጭ እያለ እንደነበር የገለፁት ምንጮች ከመለስ ጋር ምስጢራዊ ውይይት እንዳደረጉና ከመለስ ቢሮ ሲወጣ በደስታ ሲፍነከነክ እንደነበርም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ይኸው የሱማልያው ፕሬዝዳንት በመለስ ትዕዛዝ አዲስ አበባ መጥቶ ከሁለት ሰዓት በበለጠ ከመለስ ዜናዊ ጋር ምስጢራዊ ውይይት ያደረገ ሲሆን እግረ መንገዱንም የህክምና ድጋፍ ተደርጐለት እንደተመለሰ እነዚሁ የቤተመንግስት ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com